# ሰንደቅ ዓላማችን

ታሪክ ስንመረምር ወደኋላ ሄደን
ዛሬ የምንሰቅላት ይቺ ባንዲራችን
የኢትዮጵያን ውበት ልምላሜና ሀብት
ሀይማኖት ፍቅርን ጸጋና ቸርነት
መስዋዕትነትን የአላማን ጽናት
የነጻነት ትግልን ያለንን ጀግንነት
በህብረ ቀለሟ ሚስጥራዊ ክታብ
እየዘረዘረች ለዓለም በማስነበብ
ምስክር በመሆን እስካሁን ኖራለች
ትውልድን በትወልድ ደጋግማ እየተካች

ዛሬም በሚካኤል በእለተ ቀኑ
በሚታሰብበት አመታዊ ክብሩ
መድሃኒዓለም በራፍ ስዊድን ከተማ
ማየት ስለቻልን ባንዲራችን ቆማ
ምስጋና ይድረሰው ለቸሩ አምላካችን
በእልልታ ይድመቅ ይሰማ ድምጻችን

በሰፊው ሰማይ ላይ በዳመና ምንጣፍ
ሰንደቅ ዓላማችን ቀለሟ በማረፍ
ከአጥናፍ አጥናፍ ሲታይ በርቀት ሲያበራ
በዓለም ሲፈነጥቅ የቀለሙን ጮራ
ለተመለከተ ላስተዋለ በቅጥ
መገንዘብ ይቻላል ስለኛ መመረጥ

ይሄን ልዩ ውበት የተፈጥሮ ጸጋ
በባንዲራችን መልክ በዓለም የዘረጋ
ለፍጡራን አምላክ ለኃያሉ ጌታ
ምስጋና እናሰማ ድጋሚ በእልልታ

ይቺ ሰንደቃችን መገለጫችን ናት
አለን ልዩ ክብር ምንግዜም ስናያት
በእኛ ብቻ ሳይሆን በዓለም ህዝብ
ዘንድ
አላት ልዩ ማዕረግ ክብርና መወደድ
የነጻነትና የአንድነት ምልክት
መሆንዋን በማመን ብዙዎች ወደዋት
በልዩ ልዩ መልክ በቤት አሰርተው
በብዙ ሀገሮች ይታያሉ ደምቀው
እንዲሁም ባለድል እስፖርተኞቻችን
ጠላት ያባረሩ ጀግና አባቶቻችን
የመጨረሻውን ውጤት ሲቀናጁ
ማሸነፋቸውን ለአለም ሲያውጁ
ከፍ ባለ ቦታ እየተሰቀለች
ሰንደቅ ዓላማችን ደስታን አብስራለች

ዛሬም በሚካኤል በእለተ ቀኑ
በሚታሰብበት አመታዊ ክብሩ
መድሃኒዓለም በራፍ ስዊድን ከተማ
ማየት ስለቻልን ባንዲራችን ቆማ
ፈጣሪ አምላካችን ይድረሰው ምስጋና